www.ginbot7.org

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7፣ የፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

ሐምሌ 3 2000 ዓም ቁጥር 8

---

## "ደህዎች ስንመስል፣ባለፀጋዎች ነን" ሀብታሙ-ከአምስተርዳም

ቁመቱ ውፍረቱ፣ እጅግ ገዝፎባቸው፣
ዋርካን አንግሰውት፣ ዛፎች በላያቸው፣
ለክብሩ ሲሰግዱ፣ ከፊቱ ስር ወድቀው፣
እጅግ ሲያወድሱት፣ አለቅጥ ተጨንቀው፣
ከዕለታት አንድ ቀን፣ የተነሳው ዐውሎ፣
ዕፅዋቱን አልፎ፣ ዛፉን ሁሉ ዘሎ፣
ዋርካውን አስተኛው፣ ከስሩ መንግሎ፣
ዛፎች ደነገጡ፣  በአለቃቸው መውደቅ፣
ወደ ዋርካው ሄዱ፣ ነገሩን ለማወቅ፣
ግዝፈቱን በማየት፣ ያነገሱት ዋርካ፣
ትል የቦረቦረው፣ ባዶ ነበር ለካ።

ሰውየው፤ የንብን ቲሸርት ለብሰው ለ"ዝንብ" ሲቀሰቅሱ ያየሁዋቸው ዕለት ምሽቱን የፃፍኳት ግጥም ነች።በእርግጥም የዛሬን አያድርገውና ከነ አያሌ ጉድፋቸውም ቢሆን በሰውየው ያልማለለ ማን ነበር?በእርግጥም "የኢትዮጵያ መሪ ማነው?አል-አሙዲ?ወይስ መለስ?ብለው እስከመጠየቅ የደረሱ ስንቶች ነበሩ?"
"በምርቅዝ ቁስላችን ውስጥ ለምን እሾህ ትሰድብናለህ?"ተብዬ ካልተወቀስኩ በስተቀር፤ይህችን ግጥም የፃፍኳት "ቆመን የሰቀልነውን ቁጭ ብለን ማውረድ አቃተን" ብለው መተረት ለጀመሩት ለቀድሞው የሰውየው አፍቃሪዎች መፅናኛ ትሆን ዘንድ ነው።
ብዙዎች፤ ሰውየውን እስከማምለክ ደርሰው የነበረው እንዲሁ በግርድፉ "በደሀዋ አገራችን ላይ በርካታ መሰረተ-ልማቶችን ገንብተዋል፣በተሰማሩባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለዜጎች የስራ ዕድል ፈጥረዋል" ከሚልና ግራ ቀኙን ካላገናዘበ ሀሳብ በመነሳት ነበር።በሌላ አነጋገር ሰውየው፤ የኢትዮጵያንና የህዝቦቿን መከራ በማራዘም የአገሪቱን ሀብት እንደጥገት ላም ለማለብ ከገዥዎቻችን ጋር "ኒካ" ማሰራቸውን ገና በጧቱ የተገነዘብነው በጣም ጥቂቶች ነበርን።በእርግጥ በስመ-ዲሞክራሲ አምባገነናዊ መንገድን የሚከተሉ ገዥዎች፤በ"ባለሀብት ስም" እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ምስጢራዊ የጋብቻ ውል መፈፀማቸው የተለመደ ነው። የፖለቲካ ተንታኞች እንደነዚህ ዓይነቶቹንባለሀብት ተብየዎች፤"በመንግስት ውስጥ ያሉ መንግስታት (ስቴትስ ዊዝ ኢን ስቴት)"ይሏቸዋል።
የኔታ፡-" ኩሉ ፃድቅ በጊዜ ርቱዕ" እንዲሉ፤እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በአገር ውስጥ የሚነፍሰው ፖለቲካዊ አየር፤ የጋብቻ ውል ላሰሩለትና ላሰረላቸው መንግስት
የሚያሰጋ ሆኖ እስካላገኙት ድረስ፤ በባለሀብት ስም ራሳቸውን ደብቀው ትንሽ ይሰራሉ፤ብዙ ይዘርፋሉ።በማንካ ሰጥተው በአካፋ ይወስዳሉ።

ጥቂቷን ግብራቸውን፤ ህዝብ በቀላሉ ሊያየውና ሊሰማው በሚችለው ነገር ላይ እንድትሆን ስለሚያደርጉም፤ ከባዱ ሽፍጥና ስርቆታቸው በጥቃቅን ነገሮች የሚጻፈንበት አጋጣሚ ይበዛል።ለትውልድ የሚበቃውን የሻኪሶን ወርቅ እያረሱ፤ አሊ ረዲን(የቡና ገበያ ጎል ጠባቂን) ደቡብ አፍሪካ ማሳከማቸውን እንደሚያስወሩት ማለት ነው።አዎ! በሁሉም ክልሎች ማለት በሚቻልበት ሁኔታ፤ በ"ልማታዊ ባለሀብት"

ስም ጋሻ መሬት እየተገነደሰ ለሰውየው ሲሰጥ፤ ብዙዎች ሲያወሱ የነበረው ሰውየው ለዘፋኝ ሰርግ የሚኒባስ ጥሎሽ ስለመስጠታቸው ነበር።ዓይናችን ከአደናጋሪው የሸራተን ርችት ባሻገር ያለውን ሀቅ ማየት ባለመቻሉ፤ ርኩሱን-ቅዱስ፤ተኩላውን-በግ ስንል ከርመናል።

ስለ ሸራተኑ፣ስለ ዳሸኑ፣ስለ ሳራ አምፖሉ፣ስለ ብረታ ብረቱ፣ስለ ማምኮው፣ስለሜድሮኩ፣ሰለ ሲሚንቶው፣ስለፔፕሲ ኮላው፣ስለ አግሮ ኢንዱስትሪው፣ስለ ሰላም ነርስ ት/ቤቱ፣ስለ ፒያሳው ግንባታ፣ስለማይከፈለው ግብር፣ስለ ብ.አ.ዴ.ኑ፣ስለ ህ.ወ.ሀ.ቱ፣ስለ ኦ.ህ.ዴ.ዱ፣ስለ ደ.ኢ.ህ.ዴ.ጉ…ወዘተ ዝርዝር ውስጥ አልገባም።

በአጭሩ ለማለት የፈለግኩት ሰውየው፤ በስሙ-ነፃ ገበያ የአገሪቱን የንግድ ዘርፎች በህገ-ወጥ መንገድ ከተቆጣጠሩት ህገ-ወጥ ገዥዎቻችን ጋር በመመሳጠር፤ ከነአካቴው እያቆረቆዙን እንጅ እየሰሩልን አይደለም።በጣም ውስን የሆነው አገራዊ ሀብታችን በጥቂቶች እጅ እንደሚገኝ ‘ፒስ ፈንድ’ የተሰኘው ድርጅት ሰሞኑን ይፋ ያደረገው ጥናት ያሳያል።

“ልማታዊ ባለሀብት”በሚል ለምድ ስር ተደብቀው የአገርና የህዝብ ሀብት ሲመዘብሩ የሚኖሩት እንደዚህ ዓይነት ሰዎች፤እውነተኛ ማንነታቸው የሚገለጠው ወይም(ስቴት ዊዝ ኢን ስቴት መሆናቸው)ይፋ የሚሆነው፤በቃል ኪዳን የተሳሰሩት መንግስት ህልውና አደጋ ላይ ሲሆን ነው።ያኔ “ባለሀብት” የተሰኘው ሀሳዊ ለምድ ይወልቃል።የወትሮው ትህትናዊ ካባ ይገፈፋል፤ይሉኝታ “ዕንጦርጦስ ግባ!”ይባላል።የአስቴር አወቀ ሙዚቃን ሲያቀነቅን የከረመው አንደበት፤ለስድብ ይከፈታል። በሀመልማል ዘፈን እስክታ ሲል የከረመው ትከሻ ፤ለፀብ ይንጎራደዳል።ፍቅርን ሲሰብክ የከረመ አፍ፤ የበከተና የተጠላ ፖለቲካን ማነብነብ ይጀምራል።ያኔ፤ገዥውን መንግስት ከውድቀት ይታደጋል ተብሎ የታሰበ ነገር በሙሉ በደመ-ነፍስ ይደረጋል።ጊዜው ለነሱ የድንጋጤ ስለሚሆን ነው በደመ-ነፍስ ያልኩት።_ልክ ቅንጅት በምርጫው እያሸነፈ ሲመጣ ሰውየው የንብን ቲሸርት ለብሰው አደባባይ እንደውጡት ፤ወጥተውም ብዙ እንደዘላበዱት ማለት ነው።ምክንያቱም የ”ሀብታቸው”ህልውና ፤ ካለው ገዥ መንግስት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። የምርጫውን ግርግር ተከትሎ እንዲቋቋም የተደረገው ተለጣፊ የወጣቶች ማህበርም፤ ለኢህአዴግ ይቀሰቅስ ዘንድ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲወጣ ፤ከሰውየው የ 2 ሚሊየን ብር ስጦታ እንደተበረከተለት ዐይተናል።የጊዮርጊስ ስፖርት ክለብን ቀስ ብለው ከተቆጣጠሩት በሁዋላ እንዴት የገዥው ፓርቲ መቀስቀሻ ሊያደርጉት እንደሞከሩና የስፖርት ቤተ-ሰቡን እንዳስቀየሙ ዐይተናል።እንግዲህ ሰሞኑን በሰሜን አሜሪካ ለሚገኘው ለኢትዮጵያውያን እግር ኳስ ማህበር የ 300 ሽህ ዶላር ስጦታ ማበርከታቸው የዚሁ ቅጥያ መሆኑ ነው-ገዥውን መንግስት የማዳን ዘመቻ።

የሰሜን አሜሪካው ስመ-ጥር የእግር የእግር ኳስ ማህበር ዝናውን፣ክብሩንና ጥንካሬውን ይዞ ለመቀጠል የሚፈልግ ከሆነ ሰሞኑን በተበረከተለት ስጦታ ዙሪያ ጉዳዩን ግራና ቀኝ ዐይቶ በአስቸኳይ ተገቢውንና ብዙሀን ኢትዮጵያውያን የሚሹትን ውሳኔ ማሳለፍ ይጠበቅበታል።እዚህ ላይ ማህበሩ ስል የማህበሩን አመራሮች ማለቴ ነው፡፡እንዲሁ ላይ ላዩን ስጦታውን መቀበል ምን አለበት?በሚል ማደናገሪያ ነገሩን አድበስብሶ ማለፍ ስህተት ይሆናል።ምክንያቱም ሰውየውን ካለፈው ታሪካቸው እንደተረዳናቸው፤ የሚያስቡት በጭንቅላታቸው ሳይሆን በገንዘባቸው ነው።የህዝብ ሀብት ወደሆነው ወደአንጋፋው የጊዮርጊስ ስፖርት ክለብ አልፍኝ፤ በእጃቸው(በብራቸው)ሰተት ብለው ከገቡ በሁዋላ ፤በክለቡ መድረክ ላይ ቅንጣት ታህል ይሉኝታ ሳይዛቸው ህዝብ የተፋውን ፖለቲካ የሰበኩ ሰው፤ዛሬ የ300 ሽህ ዶላር ማኖ ያስነኩትን ማህበር እልፍኝ፤ ነገ ጢት የፖለቲካ መፀዳጃቸው እንደማያደርጉት ምን ዋስትና አለ? ደግሞ የእግር ኳስ ማህበሩ ሀብት፣ ውበትና ታላቅነት አገር አቆራርጦ ሳይቀር በበዐሉ ለመካፈል ከያለበት የሚመጣው ብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ እንጅ፤ዛሬ “በእጃቸው” የመጡ ሰዎች አይደሉም።ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ላይ” ለስጦታ ተብሎ” ከብዙሀኑ ፍላጎት ውጭ የሆነ ውሳኔ ማሳለፍ፤ከአራት ሰዓት በሁዋላ በእዳሪ መልክ ለሚወጣ ምስር ወጥ ብኩርናን እንደመሸጥ ነው።ደግሞም እደግመዋለሁ፤ የማህበሩ ሀብት እኛ”ሀብታሞቹ’ኢትዮጵያውያን እንጅ፤ የአዕምሮ ደሀ የሆኑ ባለ ብሮች አይደሉም።

“ደካሞች ስንመስል ሀይለኞች ነን፤ሙታን ስንባል ለሌሎች ህይወት እንሰጣለን፤ደሀዎች ስንባል ባለፀጋዎች ነን፤ምንም የሌለን ስንመስል ሁሉም የኛ ነው”ያለው ማን ነበር?